በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 6


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com


***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መጋቢት ፲፱ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 6

## ታዛዥነት

- ታዛኝነት የሁሉም ይልቁኑ የወጣት ወንዶችና ሴቶች ፈተና ነው፡፡ በተወሰነ መልኩም ታዛኝነትን የበታችነት ምልክት አድርገው የሚቆጥሩት ሲሆን በታዛኝነት መኖርም በእስር ቤት ውስጥ እንደመኖር አድርገው ይወስዱታል፡፡
- ይሁን እንጂ በክርስቶስ በሆነ ጋብቻ የሚገለጥ መታዘዝ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር መግለጫ ከመሆኑ በተጨማሪ ከመንፈሳውያን ፍሬያትም መካከል አንዱ ነው፡፡
- እግዚአብሔርን ስንወደው ትእዛዙን እንጠብቃለን፡፡ ‹‹ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡›› *ዮሐ 14፡21፡፡*
- ወላጆቻችንን ስንወዳቸው ትእዛዛቸውን እንፈጽማለን፡፡ ‹‹አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡›› *ዘጸ 20፡12፡፡*
- የንስሐ አባታችንን ስንወድ እንታዘዛለን፡፡ ‹‹ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኀዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ፡፡›› *ዕብ 13፡17፡፡*

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

## ታዛዥነት

- ፍጹም ትሑታን ሆነን ከተገኘን እየታዘዝን መገኘት እጅግ የቀለለ ይሆንልናል፡፡ ‹‹እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡›› *ቀዳ ጴጥ 5፡5፡፡*
- የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥልጣን፣ በመለኮትና በኀልውና ከአባቱና ከባሕርይ ሕይወቱ ጋር አንድ ሆኖ ሳለ የሰው ልጅ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ መባልን በመታዘዝ እንዴት እንደተቀበለ በመረዳት ከርሱ እንማር፡፡
- ‹‹ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው፡፡›› *ዕብ 5፡8-9፡፡*
- ልቦናችን በትሕትና የተሞላ ከሆነ ሰዎችን ይልቁኑ የትዳር አጋራችንን ማክበር እጅግ የቀለለ ይሆንልናል፡፡ በርግጥ ማንኛውንም ነገር ወይም ሁኔታ በጭፍን እንድንታዘዝ አንገደድም፡፡ ሕይወታችንን መምራት የሚያስችለንን ብቃት ይሰጠን ዘንድ ነገሮችን ሁሉ በሠለጠነ መልኩ በጸጥታና በርጋታ ሆነን ጥበብና የመመምራት አቅምን የሚያድል እግዚአብሔርን እንጠይቅ፡፡

## ታዛዥነት

- መታዘዛችን በተፈለገበት ጊዜና ቦታም ታዛዦች ሆነን እንገኝ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መታዘዛችን የትዳር አጋራችንን ደስ ለማሰኘት ያለንን ቁርጠኝነት የሚጠቁም ሊሆን ስለሚችል ለምን እንደምናደርገው በግልጽ ባይገባንም እንኳ የምናደርገው ከጌታችን ፈቃድ ጋር እስካልተጋጨ ድረስ እናድርገው፡፡
- አንዳንድ ሰዎች መታዘዝን ከደካማነት የመነጨ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ጌታችን መታዘዝን ስለምን አድርጎት በተግባር እንዳስተማረን ስንረዳና ስናደርገው ግን ለትዳራችን የሚጠቅም ደስታንና ድልን እንጎናጸፋለን፡፡
- ስለዚህ ባልና ሚስት እርስ በርስ ለመከባበር ፈጣኖች መሆን ያስፈልገናል፡፡ አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ ሲል በመናደድ በሚናገረው ኃይለ ቃል አማካይነት ክፋት (ሰይጣን) አሸናፊ ሆኖ በመካከል ይገባ ዘንድ አንፍቀድለት፡፡
- አለመግባባት በሚፈጠርበትም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ‹‹ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፡›› *ኤፌ 5፡24፡፡* በማለት ያዘዘውን ሚስቶች ሁሉ ፈጽሙ፡፡
- ሚስቶች ሆይ! ‹‹እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው፡፡›› *ቀዳ ጴጥ 3፡1-2፡፡* እንደተባለ ዘወትር ለባሎቻችሁ ለመታዘዝ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

## ታዛዥነት

- ባሎች ሆይ! ራሳችሁን በፍጹም ደስታ ለሚስቶቻችሁ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡
- ባሎች ሆይ! ሚስትም ነጻነትዋን እንደጠበቅንላት ሳናስቆጣትና ሳናበሳጫት እንድትታዘዘን ጥበብና ፍቅርን እንጠቀም፡፡
- ባሎች ሆይ! ይህንም ስታደርጉ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ›› *ኤፌ 5፡25፡፡* በማለት ያስተማረውን ትምህርት ተከትላችሁ ፈጽሙ፡፡
- እያንዳንዳችሁም በጋዛ ራሳችሁ ሐሳብ ላይ ሳትጣበቁ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ታዘዙ፡፡
- በክርክሩ የሚረታው ወይም አለቃው ማነው ብላችሁ አታስቡ፡፡ ምክክራችን ሁሉ ራሳችንን ሳይሆን የትዳር አጋራችንን ደስ ለማሰኘት ዝግጁነታችን የሚገለጥበትና ፍቅራችንም የሚነበብበት ይሁን፡፡
- ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ መታዘዝ ያለብን ለእግዚአብሔር እንደሆነ በመቀጠልም ለትዳር አጋራችን መታዘዝ እንዳለብን በማስከተልም ለወላጆቻችንና ለሌሎች በመጨረሻም ለራሳችን መታዘዝ እንዳለብን እናስተውል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

**ታዛዥነት**

መታዘዝ

- በቅድሚያ ለእግዚአብሔር
- ሁለተኛ ለትዳር አጋራችን
- ሦስተኛ ለወላጆቻችን
- አራተኛ ለሌሎች
- አምስተኛም ለራሳችን ነው

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

## ጽንዓት

- ጽንዓት ቁርጠኝነት ወይም የማያቋርጥ ጥረት ማለት ነው፡፡
- የሚያፈቅር ሁሉ ምንም ነገር ቢፈጠር በፍቅሩ ‹‹ጽኑእ›› መሆን ይገባዋል፡፡ ‹‹በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ፡፡ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፡፡ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም፡፡ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል፡፡›› *ቀዳ ቆሮ 13፡1-7፡፡*
- ጌታችን ስለሚወደን ዘወትር ወደ ዘላለማዊ መንግሥቱ ይመራን ዘንድ ይሠራል፡፡ እንደ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ያለውን ሳያቋርጥ በጽንዓት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ የሚሠራልን የለንም፡፡ እግዚአብሔር ዓለሙን በመውደድ አንድያ ልጁን የሰጠንም በሱ የተነሳ ስለመዳናችን ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

## ጽንዓት

- አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ በሚያሳየው ትዕግሥቱ እጅግ እንደነቃለን፡፡
- ክፉዎች ሰዎችን እንኳ ወደራሱ መንግሥት እስኪያቀርብ ድረስ እግዚአብሔር ስላሳየው ትዕግሥትና ጽንዓት በቤተ ክርስቲያን ዘወትር እየሰማንና እያነበብን እንገኛለን፡፡ ለቅዱስ ጳውሎስ፣ ለቅዱስ አውግስጢኖስ፣ ለኢትዮጵያዊው (ጸሊም) ሙሴ እንዴት ያለ ትዕግሥቱን አሳይቶናል!!!
- ዮናስም ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ ‹‹አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው፡፡›› *ዮና 4፡3፡፡*
- እንደዚሁ በእግዚአብሔር ፍቅር ነፍሱ የጠገበች ሰው ፍጹም ትዕግሥት አለው፡፡
- ሙሴ አስቀድሞ ፈጥኖ የሚናደድ የሚቆጣ ደመ - ትኩስ ነበር፡፡ ስለ ወገኖቹ ቁጭት ሲል ግብጻዊውን ገድሎ በአሸዋ ውስጥ ቀብሮታል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በፈቃዱ እየተመራ ቆይቶ ደግሞ ስላሳየው ትዕግሥት … ለሕዝቡ እንደማለደ ተጽፎልናል፡፡ ***ዘጸ 32፡32፡፡***
- ትዕግሥትና ጽንዓት ለማንኛውም ትዳር ስኬታማነት ቁልፍ ነገር ነው፡፡
- በክርስቶስ በሆነ ትዳር እግዚአብሔር ለትዳራችን ፍጹም ሰላምን፣ ዕድገትንና ደስታን እንዲያድል ዘወትር በጸሎት መጠየቃችን እንደመንፈሳዊ ተግባርና ትእዛዝ የሚቆጠር ነው፡፡
- በሌላ በኩል የትዳር ታላቁ ጠንቅ ቁጣና ብስጭት ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6

## ጽንዓት

- እንደሌሎቹ መንፈሳዊ ሀብታት እግዚአብሔር ትዕግሥትን ይሰጠን ዘንድ በጸሎት ተግተን መጠየቅ የሚጠበቅብን ከመሆኑ በተጨማሪ ይህ ምግባር ተዋሕዶን ይኖር ዘንድ ትዕግሥትን መለማመድ ያስፈልገናል፡፡
- የትዳር አጋራችን ፈጥኖ-ተናዳጅ እንደሆነ ወይም እንደሆነች የሚከተሉትን ነገሮች እናድርግ፡-
    - ስለርሱ ወይም ስለርስዋ እንጸልይ
    - በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ሌሊት ለውጥ ለማምጣት አንሞክር
    - የበዛ ፍቅርን፣ ክብካቤንና ድጋፍን እናሳይ
    - ለመለወጥ በሚያደርጉት ጥረት ሁሉ እንተጋገዝ
    - ሊያስቆጣው/ሊያስቆጣት የሚችለውን ነገር ሁሉ በመቆስቆስ ጠብን የሚያባብስ ነገርን ከማድረግ እንቆጠብ
    - ከመጠቋቆምና ከማስጠንቀቅ እንራቅ

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 6</u>

**ጽንዓት**

- ድካሙን/ምዋን ወይም ያለበትን/ያለችበትን ሁኔታ ባግባብ የተረዳን እንሁን
- የሚሠራውን/የምትሠራውን ደካማ ነግር ካለመውደድ የተነሳ ለመለወጥ የሚጣጣሩ መሆኑን እንወቅ፡፡

- በጸሎትና በትዕግሥት ጸንተን ስንሰራ ነገሮች በጊዜያቸው ተገቢውን አቅጣጫ እንደሚይዙ እንወቅ፡፡
- የማንፈልገውም ነገር ሲሰራ በትዕግሥት ትኩረትን ሰጥተን ነገሩን ወደ ጤናማ መንገድ ለመምራት እንጣጣር እንጂ ማንንም ሊጠቅም ወደማይችል ጩኸት ወይም ራስን የመነቅነቅ ተግባር የምንዘፈቅ አንሁን፡፡ ይህም አካሄድ ማንንም የመርዳትም ሆነ ችግርን የመፍታት አቅም የለውም፡፡
- ‹‹የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች ሸካራ ቃል ግን ቍጣን ታስነሣለች፡፡›› *<u>ምሳ 15፡1፡፡</u>* እንደተባለ እናስተውል፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org